# ይድረስ ለጋዜጠኛው ማስታወሻ ደራሲ፡፡

**ከወይናና 02/27/09**

ይድረስ ለምርኮኛው ማስታወሻው ባንተው አባባል “የጋዜጠኛው ማስታወሻ፤ ደራሲ”:: ይኸው አይን ለአይን መተያየት ካቋረጥን 8 ዓመታት ሊሞላን ነው። ልቦና ላለው ሰው ስምንት ዓመታት ብዙ ቁም ነገር የሚቀስምባቸው: ቢያንስ ቢያንስ ራሱን በሚገባ ሊገነዘብ የሚያስችሉት ዓመታት ናቸው። ሆኖም የጅል ነገር (ደራሲው ራሱ ካለው የወሰድኩት ነው) ሆነና እነሆ ከስምንት ዓመት በኋላም እንዲሁ ጥሬ ነህ። ጥሬ ብቻ ሳትሆን አዲስ የፈጠራና የማስመሰል ችሎታም ጨምረህበታል። ፈጠራ ስልህ በአወንታዊነቱ እንዳይመስልህ::

በነዚህ ስምንት ዓመታት ውስጥ የት እንደነበርክ የማውቀው ነገር አልነበረኝም። ቂም እንዳትይዝብኝ አደራህን እየጠየኩ ለምን እንዳላወኩ ወይም ለማወቅ እንዳልተገደድኩ ግን በትንሹ ላብራራልህ።

የምሬን ነው የምልህ ተስፋዬ። አንተ በእኔ ዓይን ሁሌም ምርኮኛ ነበርክ። ቅንጭብጫቢ ፀሀፊነትህን የማደንቅ ብሆንም አንድ ጊዜም ቢሆን እንደ ቁምነገረኛ ታጋይ ፤ እንደ ዓላማ ያለው ሰው አድርጌ አስቤህ አላውቅም። በስብሰባዎች ላይ አብረን ስንገናኝ የመነጋገሪያ አጀንዳዎቻችን ግራ አጋብተውህ መሃሉ ላይ ስትዘባርቅ ሳቄን በሰፊው ላለመልቀቅ የተቸገርኩባቸው ወቅቶች በርካታ ነበሩ። አሁንም ደግሜ ደጋግሜ ልንገርህ፤ የወሬ ለቃሚነት ሱስ ኖሮብኝ ስለ ተስፋዬ ምን ታስባላችሁ ብዬ ሌሎች ጓዶችን ጠይቄ ባላውቅም አልፎ አልፎ በየስብሰባው ሲነሱ ከነበሩት አስተያየቶች የምገነዘባቸው ቁምነገሮች ግን ሁለት ነገሮችን የሚያመለክቱ ነበሩ። ተስፋዬ ዛዲግም፤ ሞኝም ነው የሚሉ ናቸው። ዛዲግን ታውቀዋለህ? አዎ ብዙ መፃሕፍትን አንብቤያለሁ የሚል ኑዛዜ ስለገባህ፤ እድለኛውን ዛዲግ ሳታውቀው አትቀርም። ካላወቀው ቻለው። ባጭሩ ግን ዛዲግ እዳንተው ዕድለኛ ነበር። አቶ ሙሉጌታ ሉሌን ረገምከው ወይም አመረርክበት እንጂ ያኔ ገና ወደ ወታደሩ ቤት ሳትገባ በሪፓርተርነት ቢቀጥርህ ኑሮ ምን ልትሆን ትችል እንደነበር ገምት።

ስለዚህ በእኔ ዓይን ሁሌም ምርኮኛ ነበርክና የት ገብቶ ይሆን ብዬ ላፍታም ቢሆን አስቤ አላውቅም። አንድ እርግጠኛ የሆንኩበት ነገር ቢኖር በርካታ ብሮችን ይዘህ መጥፋትህንና ያንን ብር እየበተንክ በህሊና ቁስል እየተሸማቀቅክ ትኖር ይሆናል የሚል ግምት  ያኔ በተሰወርክ ሰሞን አስቤ እንደነበርኩ ግን አልዋሽህም። በዚያ ሰሞን በሰው በረት ገብቶ እየባነነ እንደሚያድር ወይፈን ከምትሆን ሽሽትን መምረጥህ አሳምሬ አውቀዋለሁ። ለካ አጅሬ ግን ጎበዝ ኖረሃል። ያችን የመነተፍካትን ብር ይዘህ ባለ ኢንተርኔት ካፌ ለመሆን በቅተሃል፤ ታድያ ይኸው ሳይበቃህ አሁንም ሌላ አዲስ ዘዴ ዘየድክ። ቅንጭብጫቢ ተረት ተረቶችን ማሰባሰብና ማሳተም፤ በዚያም እንደገና መክበር።

በል እንግዲህ ተስፋዬ፣ እኔ ይህን ፅሑፍ ለመፃፍ የተገደድኩት አሁንም በድጋሚ ልንገርህና አንተን እንደቁምነገረኛ፣ ባለወጥ ሀሳብ አይቼ እንዳይመስልህ። በፍፁም። እኔን የነካካሽኝ መስሎህ የሰጠሁት ምላሽ እንዳይመስልህም አደራ። ያም ሆኖ ግን፡

- ራስህን እንደ ጲላጦስ ከምንም ነገር የፀዳህ አስመስለህ በመመፃደቅህ፤
- ከአገር የወጣህበትን ምክንያት ፖለቲካዊ ይዘት እንዳለው አስመስለህ ተክለሰውነትህን ለማሞገስ በመሞከርህ፤
- መላ ምቶችንና ሃሜቶችን እንደ ጭብጦች በመጠቀም ተነባቢውን በማደናገርህ፤
- ከሁለም በላይ ግን እነዛ ሰማእታት ተስፋይ ለማ ፣ ዙፋን ፍስሐ እንደዚሁም አሁን የት እንዳለ የማላውቀው ሻምበል ፈቃደ የተፈፀመባቸው በደል መታለፍ የለበትም ብዬ በማመን ይህን አጭር መልስ እንድፅፍ አስገድዶኛል ።
- 

## <u>ተስፋዬ ገብረ አብ ማነው?</u>

ደብረዘይት ተወለድኩ፤ ሪፖርተርነት ልቀጠር ማመልከቻዬን ለአቶ ሙሉጌታ ሉሌ አቀረብኩ፤ ተስፋ ቆርጬ ወታደርነት ተቀጠርኩ፤ በደርግ ውድቀት ዋዜማ

ደብረታቦር ተማረኩ፤ በመጨረሻም ''ትልቅ'' የኢህአዴግ ባለስልጣን ሆኜ ከሁለት ዓመታት በኃላ አ/አበባ ተመለስኩ የሚለውን ተረት ተረት አንተው ስለተረከው አልመለስበትም። ከምርኮኝነትህ በፊት የማውቀው ነገር ስለሌኝም የምለው ነገር አይኖረኝም።

አንተን የማውቀው እዛው እፈረደበት ''ሃገረሰላም'' ነው። በመፅሐፍህ ውስጥ ''ኢዴመአንን'' ለምን እንደረሳኸው አልገባኝም። አዎን ለአንባቢያን ግልፅ ለማድረግ ኢዴመአን ( የኢዮትዮጰያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ) በመባል የሚታወቅ ስብስብ ነበር። ከዚህ ስብስብ ውስጥ ለኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ውለታ የሰሩ ጀግኖች እንደነበሩበት ሁሉ እንዳንተ ዓይነቱ ሰውም ነበረበት። ወቅቱ ስለረዘመ ወራቱን በትክክል ባላስታውሰውም በ82 ዓ.ም አጋማሽ አካባቢ በአንዲት የእንጨት ፍልጥ ላይ ኩርምት ብለህ ከጀሪካን ቅዳጅ( ራሕባ) በተሰራ ሰሐን ምግብ ስትበላ እንዳገኘሁህ ትዝ ይለኛል። የኢዴመአን ታጋይ ነው፤ በኢዴመአን ስም የሬድዮ ፕሮግራም ስለሚዘጋጅ ያንን ለማዘጋጀት ነው የመጣው የሚል መረጃ የተነገረኝ በተወዳጁ ሟች ጓድ ገብረ መስቀል ሃይሉ ነበር።

ያን ወቅት አትስተውም፣ የዘመቻና የድል ወቅት ነበር። የትጥቅ ትግልና የዲፕሎማሲ ትግል ጫፍ ላይ የደረሰበት ወቅት ነበር። ደርግ ከሻዕቢያ ውጭ ሌላ ተቃዋሚ የለም ሲል በነበረው አንደበቱ ኢህአዴግ የሚባል አገር በቀል ጠንክራ ድርጅትም አለ ለማለት የተገደደበት፤ ከህወሓት ጋር ብቻ ሳይሆን ከኢህዴን ( ያሁኑ ብኣዴን) ጋርም በኢህአዴግ ስም እደራደራለሁ ያለበት፤ ጭፍጨፋና አፈና የበዛበት፣ የኢትዮጰያ ህዝብ የኢህአዴግን ጮራ በቅርብ መመልከት የጀመረበት ወቅት ነበር። ምን ይህ ብቻ! ደርግን « አትገድልም ወይ? » እያሉ መመሪያ ሲሰጡ የነበሩት አሁን የተንበረከከላቸው ፕሮፌሰሮችም ደርግን አፍ አውጥተው የተቃወሙበትና የህዝቡን ትግል ለመንጠቅ የአደራ መንግስት እንዲቋቋም ጥሪ ያቀረቡበት ወቅትም ነበር። አንተ እንኳ የአንድ ሳምንት ወታደር ስለነበርክ ብዙም አታውቀውም እንጂ የአንተ የበላይ በላይ አለቃዎች በሰላም ለኢህአዴግ እጃቸውን መስጠት እንደ ቀልዳ ቀልድ የሚታይበት ወቅት ነበር።

በዚህ ወቅት የመጣው ተስፋዬ ገብረ አብ አቶ አማረ አረጋዊ በመራው ጉባኤ ኢ.ዴመአን ተመሰረተና የዚህ ድርጅት የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ሆነ። አዎ እዚያው ሀገረሰላም አካባቢ በተደረገው ጉባኤ ከትቢያ ተነስተህ የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ሆንክና በሚዲያ እንድትሰራ እኛ ጋር ተመበድበህ መጣህ። ሁለት ወራት ብቻ የደርግ ወታደር ሆኖ ያገለገለ አንድ ቂላቂል ወጣት እነሆ የአንድ የመኮንኖች ድርጅት ማእከላዊ ኮሚቴ አባል ሆነና የኢህአዴግ የሚዲያ ኮሚቴ አባልም ሆኖ ሀገረሰላም ተመደበ። ወቅቱ ፋታ የሚሰጥ አልነበረም። ጠዋት ቆቦ ነፃ ወጥቶ፣ ቀን ሮቢት፣ ጎብየ፣ አመሻሽ ላይ ወልዲያ ሌሊት መርሳ የሚደገምበት የነበረበት ወቅት በመሆኑ ቀን የተፃፈ ዜና፤ ግጥም፤ ሃተታ ሁለት ሶስት አራቴ የሚቀየርበት ግዜ። ከዛም አልፎ ኢህአዴግ ከደርግ ጋር ያደርጋቸው የነበሩ ድርድሮች በዚያ ኃላ ቀር የሬድዮ መልዕክት ከለንደን እየተንደረደሩ ከሀገረሰላም ሚደርሱበት፤ እነዚህ የሬዲዮ መልዕክቶች ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛና ትግርኛ ለመተርጎም ፍዳችንን ምናይበት ግዜ ነበር። ከ24ሰዓት ውስጥ ለሁለት ሰዓት እንቅልፍ ከተገኘ ተመስገን የሚባልበት ወቅት። በዚያ ቀውጢ ሰዓት ይህ ነው የሚባል ሚና ያልነበረህ ተስፋዬ የድብቅ ፍቅር የምታካሂድ፤ ነውረኛ ሰው ነበርክ። የትርጉም ትርጉም ከመስራት ውጭ ይህ ነው የሚባል ሚና ያልነበረህ ሰው።

ደርግ ወደቀና አ/አበባ ተገባ።እኔ አ/አበባ የገባሁት ዘግይቼ ነው። ከሁለት ወር በኃላ አ/አበባ ስገባ የፕሬስ መምሪያ ሓላፊ ሆነህ መመደብህን፣ እንግሊዘኛ ተናጋሪ ነጭ እንግዳ ፕሬስ መምሪያ ሲመጣ ቢሮህን ጥለህ ትደበቅ እንደነበር የወሬ ወሬ ሰምቼ ሳቂ መጨረሻ አልነበረውም። ለመሆኑ ተስፋዬ ከፕሬስ መምርያ ለምን እንደተነሳህ የገለፅክበት አጋጣሚ ሰምቼ አላውቅም። ከኔ በላይ እነ አቶ አብርሃ በላይ ያውቁት ይሆናል። የሆነ ሆኖ የችሎታ ጉዳይ መሆኑ ግን ኃላ እኔም ሰምቼዋለሁ።

ግን ተስፋዬ የዋዛ ሰው አልነበርክም። ለፕሬስ መምሪያም ይሁን ለሌላ ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን የሚመጥን አቅም እንዳልነበረህ በውል የተገነዘብከው ቀድመህ ነበር። እናም እዛው ሆነህ በፕሬስ መምሪያ ደረጃ የነበሩትን የመንግስት መፅሔቶች ከማጠናከር ይልቅ ወደፊት ዝርፊያ የምታካሂድበት

ስርዓት ዘርግተህ እፎይታ የሚል መፅሔት የማዘጋጀት እቅድ እንዳለህ አቶ አለም ሰገድን አሳምነህ « በፎርም » ሽል አልክ። አይ አራዳው። በእፎይታ መፅሔት የምታወጣውን ፅሑፍ ለምን በፕሬስ መምሪያው ስር በሚታተሙት እንደነ የካቲት በመሳሰሉት መፅሔቶች አታወጣውም ወይም ለምን ሌላ ጠንካራ መፅሔት በፕሬስ መምሪያ ውስጥ ለማዘጋጀት አትሞክርም? የሚል ጥያቄ አልቀረበብህም። ለምን መሰለህ፤ ፕሬስ መምሪያ ከአቅምህ በላይ መሆኑና በየቀኑ ነጭ ባየህ ቁጥር፤ ወደ ብርሃንና ሰላም ለሌላ ጉዳይ የመጣውን ጭምር ስታይ ደንብረህ ግቢውን እየለቀቅክ እንደምታስቸግር ኢህአዴግ ቢሮ አካባቢ በሰፊው ይወራ ስለነበር ነው። ስለዚህ ኢህአዴግ ባዶ ቦታ ላይ ሊጥልህ ስላልመረጠ ውለታ ሰራልህ። የራስህን ኢምፓየር ፈጥረህ ስትወጣ ይሁን እስቲ ተብለህ ወጣህ።

ሌላስ ምን ትዝ ይልሀል? ከረሳህ ላስታውስህ። ሻምበል ፍቃዱን ( ለግዜው የአባቱን ስም እረስቼዋለሁ፣ ይህን የሚያነቡ የኢዴመአን መኮንኖች ያስታውሱት ይሆናል) ታስታውሰዋለህ? የኤሊባቡር ልጅ ሻምበል ፍቃዱ 84ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ የኢዴመአን ስብሰባ በአ/አበባ ከተማ መካሄዱን አትክድም። ከላስታውከው ይህን ስብሰባ የመራው ተጋዳላይ ልኡል ነበር። ልኡል በርሀ፤ በትግል ወቅት « ተሓግ » ተብሎ የሚታወቀውን ዝነኛ ግጥም የደረሰ ታጋይ። ያኔ ሻምበል ፍቃዱ ልዑል አስራተ ካሳ ግቢ ውስጥ ይሰራ ነበር። በኢዴመአን ስብሰባ ወቅት በአንተ ምግባረ ብልሹነት ዙርያ  በመናገሩ ደጃች ውቤ ሰፈር አካባቢ አድፍጠህ ጠብቀህ ሽጉጥ ተኩሰህ የግድያ ሙከራ እንዳደረስክበት መችም ቢሆን አትክደውም። አቅምና ተገን ያልነበረው በመሆኑ እኔ ድጋፍ እሰጠው እችል እንደሆነ ገምቶ የደረሰበትን እያለቀሰ ነበር በነጋታው የነገረኝ። ጭራሽ ከኢህአዴግ ራዲዮ ጣቢያ ልታባርረው እንደዛትክበትም ነግሮኛል። በወቅቱ ማድረግ የምችለው አንድ ነገር ብቻ ነበር። እሱም ከኢህአዴግ ራዲዮ ጣቢያ ለማባረር የማትችልበት ሁኔታ መፍጠር። ስለሆነም ከነ አቶ ገ/መስቀል ሃይሉ ጋር ተነጋግረን ለግዜውም ቢሆን እቅድህን አበላሽተናል። የመጨረሻ መጨረሻ ግን የኢህአዴግ ራዲዮ ጣቢያ ተበትኖ ራዲዮ ፋና ከተቋቋመ በኃላ ሻምበል ፍቃዱን ለበረንዳ አዳሪነት እንደዳረከው እዚያው የግድያ ሙከራ ባደረክበት አካባቢ ተጎሳቁሎ አግኝቼው ነግሮኛል። የማንን እጅ እንደተጠቀምክ አጫውቶኛል። እንደዛ አይነቱ አሉባልታ ውስጥ መግባት ስለማልፈልግ ግን

ነገሩን በዚህ ልቋጨው።

ተስፋዬ፣ እስቲ አንድ ነገር ላስታውስህ። 84 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ የተደረገው የጋዜጤኞች ማህበር ምስረታ ታስታውሳለህ? ካለስታሰስከው እኔው ላስታውስህ። አምስት ኪሎ በሚገኘው በጀርመን ካልቸራል ኢኒስትትዩት ነበር የተካሄደው። ያኔ የግል ሚዲያዎች ብዙ አልነበሩም። የሚቹ የአቶ ታምራት በቀለ በታምቤክ ኢንተርናሽናል ስር ሲታታም የነበረው ጋዜጣ በስፋት ከሚታወቁት አንዱ ነበር። ስለዚህ የዚያ ስብሰባ አጀንዳ የመንግስት፣ የድርጅትና የግል ጋዜጠኞች ማህበር መመስረት ነበር። አንድ ላይ ሆነው ስለሙያቸውና ጥቅማቸው የሚነጋገሩበት የጋራ ማህበር መመስረት፣ ቀና መነሻ ነበረው። አሁን የሚታየው የመንግስትና የግል ማህበሮች ይመጣሉ ብሎ የተነበየ አልነበረም። ታድያ አንተ ነበርክ ነገሩን ሁሉ ያበላሸኸው፣ በፕሬስ ሚዲያ ሃላፊነትህ ወቅት የጠላሃቸውንና የናቁህ እንደነ አቶ ክፍሌ ሙላት አይነቱ ሰዎች እንደጠላት አድርገህ ሪፓርት በማድረግ እነ አቶ ክፍሌ ሙላት የኢህአዴግ ቀንደኛ ጠላቶች ናቸው ብለህ ወሻከትክ። አቶ ክፍሌ ሙላት « ትግራይ እስክትለማ ሌላው አገር ይድማ » የሚለውን ግጥም የፃፈው ከዛ በኋላ ነበር። ያም ስብሰባ አላማውን ስቶ የዚያችን አገር ጥቂት የሚዲያ ባለሙያዎች በሁለት ጎራ ፈርጆ ወጣ። አንተ ያመጣኸው ጦስ ይኸው እስከ ዛሬው የአገሪቱ ጋዜጠኞች በሁለት ጎራ ተከፍለው ሲናቆሩ እናያለን።

ተስፋይ ለማንስ ታስታውሰው ይሆን? ስላላስታወስከው አንድ ሰው ብለህ የንቀት ተረተህን ነገርከን። አዎ ተስፋይ ለማ ተማርኮ ወይም ዘፈን ሰምቶ ወደ ትግል የተቀላቀለ ሰው አልነበረም። ገና ዓዲ አቡን ውስጥ ህፃን ሳለ እንደማንኛውም የትግራይ ወጣቶች የደርግ ጥላቻና የህወሓት ፍቅር የነበረው ቢሆንም በህፃን አእምሮው ተገፋፍቶ ወደ ትግል አልመጣም። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብቶ፣ በታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪውን ይዞ በሰባዎቹ አጋማሽ ወደ ትግሉ የተቀላቀለ፣ ህወሓትን የሚያፈቅር ወጣት ነበር። ከኔ ጋር ለብዙ ዓመታት አብረን ሰርተናል። በጥናትና ትርጉም ክፍል፣ በሬድዮና በጋዜጣ አብረን የትግሉን ሙቀትና ቅዝቃዜ ተጋርተናል። ጥንቁቅና ድንቅ ተርጓሚ ነበር። ከማንበብ ይልቅ መጻሓህፍትን ማግደው ቢሞቁባቸው ይመርጣሉ አልከን እንጂ በጥናትና ትርጉም ምድባችን ወቅት ምርጥ ምርጥ ክላሲካል መፃሕፍትን ለህትመት

ባይበቁም ማንበብ ብቻ ሳይሆን ተርጉመናቸዋል። ይህ ላንተ ባዕድ ታሪክ ነው።

ወደቁምነገሩ ልመለስና ተስፋይ ለማ ጥንቁቅ ከመሆኑ የተነሳ ከዙፋን ፍሰሃ ጋር የነበረውን ፍቅር በድብቅ ይዞት ለአመታት ዘልቋል። ሃገረ ሰላም ውስጥ ስለ ፍቅሩ በጨረፍታ አውግቶኝ ለምን ይፋ አታደርጉትም ብዬ ጠይቄው፤ የደርግ መውደቂያ ወቅት እየተቃረበ ስለሆነ ያኔ ይፋ ይሆናል ነበር ያለኝ። መፃኢ ብሩህ ተስፋ እያሰበ። ግን አንተ ልክስክስ በመሃል ገባህና ለዛች መለሎ ዙፋንና ተስፋይ ሞት መንስኤ ሆንክ። ተስፋይና ዙፋን የተሰዉ ዕለት ለስራ ጉዳይ ከሄድኩበት ከአስመራ የተመለስኩበት ቀን ነበር። መርዶውን ገና ቦሌ እያለሁ ሲነግሩኝ፤ ተስፋዬ ገብረ አብ አጋደላቸው አይደል? ነበር ያልኩት። ተወው እሱን፤ ምንም አያስፈልግም ነበር የተባልኩት። ሆኖም ግን እነዚያ ለጋ ወጣቶች የታገሉለት ዓላማ ተሳክቶ ፍሬውን ሳይቀምሱ ታህሳስ 84 አስክሬናችው ወደትግራይ እንዲጫን ምክንያት ሆንክ። ዛሬም በዚ ድርጊትህ ሳትፀፀት ተመፃደክበት። ዙፋንን ወሽሜ ነበር አልከን። እውነትም ጅል።

አቶ እሸቱስ እንዴት ትዝ አላለህም? ያ ቆፍጣናው እሸቱ። ፋና አሳታሚ ድርጅት የግል ንብረት ነው ወይስ የድርጅት ብሎ ጥያቄ በማቅረቡ ምን ልታደርገው አስበህ እንደ ነበር ትዝ ይልህ ይሆናል። ለምን በቅንጭብጫቢው ማስታወሻህ እረሳኸው? እነዚያ አልታኘክ ያሉህን የፕሬስ ጋዜጠኞች በገዛ አገራቸውና ልምዳቸው የመኖር ነፃነታቸውን ነፍገህ አንዳንዶቹን በግዞት አንዳንዶቹን በቅጣት በታተንካቸው። ታሪከኛ ነህ። እናም ይኸው የተለመደው ድርጊትህ ከመንግስት ሚድያ ወደ ድርጅት ሚደያ ተሸጋገረና በአቶ እሸቱ ላይ ልትደግመው ከጀልክ። እሸቱን ከምድረ ገፅ ካላጠፋሁ ብለህ አንገራገርክ፣ ከስራ አገድከው፡፡ያኔ ግን በኢህአዴግ ልሳኖች ስር ስለነበርክ ዕድል አልተሰጠህም። ያለህ አማራጭ ከአቶ እሸቱ ጋር ተስማምተህ መስራት ብቻ መሆኑን ተነገረህ። እንደተለመደው አራት ኪሎ ሂደህ መሰሪ ውሽትህን ለመቀላመድ ሞክረህም አልተሳካለህም። የመጨረሻ መጨረሻ የተሳካልሀ ነገር ቢኖር እነ አቶ እሸቱ የደከሙበትን ገንዘብ እና ለጡረታ ያጠራቀሙት ፕሮቪደንት ፈንድ ጭምር ይዘህ መኮብለል ብቻ ሆነ። ይህን በኋላ ስለምመለስበት ትእግስቱን ይስጥህ።

እንግዲህ ተስፋዬ ማነህ የሚለውን ላጠቃልል። ተስፋዬ እንደ ዛዲግ ዕድል

ገጥሞት ያልዘራውን ያጨደ ግለሰብ ነው። በኔ እይታ ተስፋዬ ከአቅሙ በላይ ሹመት አግኝቶ ከአቶ ክፍሌ አድነይ (በነገራችን ላይ አቶ ክፍሌ አድነይ አንድ ግዜ አስመራ አግኝቻቸው «ያን ተስፋዬን እዛ መመደባችሁ ትክክል አልነበረም፤ አቅም አልነበረውም፤ እንደዛ ዓይነት ቦታ በሱ አይነት ሰው መመራት አልነበረበትም ብለው አጫውተውኛል») ጉያ ስር ለመደበቅ ቢሞክርም ያልተሳካለት፤ ነጭና እንግሊዘኛ ተናጋሪ ባየ ቁጥር ሲደነብር የኖረ የመጀመሪያው ጥፍጥፍ መሃይም የኢትዮጵያ የፕሬስ መምሪያ ሓላፊ ነበር። ተስፋዬ የተሰጠውን ሃላፊነት እንደማይችለው ገምቶ ሌላ ምጣድ ጥዶ እንጀራውን በፋና ዲሞክራሲ ስም የጋገረ መሰሪ ነበር። ተስፋዬ ራሱ የተናዘዘውን ብቻ እንኳ በማጣቀስ የፕሬስ ሰዎችን በቂም በቀል ከጡረታና ከኑሯቸው የበተነ ሰው ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር የታገሉ (ታግያለሁ የሚል ከሆነ ) ጓዶቹንም በሸጉጥ ለመግደል ወደኋላ የማይል ጨካኝ አውሬ ነው። ተስፋዬ የራሱን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ ሲል ከመምሪያ ኃላፊነት ወርዶ ወሬ ለማቀበል የተሰማራ አሳባቂ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ጋዜጠኞች ለመከፋፈል መንስኤ የሆነ መሰሪ የጭቃ እሾህ ነው። ተስፋዬ ገብረአብ የሁለት ለጋ ወጣቶችን ፍቅር ያፈናቀለ ብቻ ሳይሆን ህይወታቸውንም ባጭር እንዲቀጭ ምክንያት የሆነ የውስጥ እግር ቁስል ነው። ተስፋዬ ገብረአብ ከጥቅሙ ፊት ለፊት የቆመውን ሰው በማንኛውም መንገድ ለማጥፋት ወደኋላ የማይል አረመኔ ነው። ምርኮኛው ተስፋዬ ባጭሩ ይህን ይመስላል።

## የቡርቃ ዝምታና ማንነትህ፡

እኔና አንተ በአንድ ላይ የሰራንበት ወቅት ባይኖርም አንተ እየወሻከትክና የራስህን ኢምፓየር እየመሰረትክ መሆኑን ከተደረሰበት በኋላ የኢህኤግ ልሳኖች አደረጃጀት ኮሚቴ ውስጥ ለጥቂት ሳምንታት ቢሆንም በአንድ ኮሚቴ ውስጥ ሰርተናል። የዚያ ኮሚቴ አላማ የኢህአዴግን ልሳኖች የጋራ አቅም የማስተባበርና የማቀናጀት ሲሆን፤ ኮሚቴው የጋራና የተናጥል እቅዶችን እያወጣና እየገመገመ ሲሰራ ቆይቷል። የጉደኛው ተስፋዬን ዓቅምና የውስጥ ኢምፓየር በቅርበት ለማወቅ የተቻለውም በዚህ ወቅት እንደነበር አትክድም።

በርግጥ ተስፋዬ እዚህ ኮሚቴ ውስጥ ላለመግባት ብዙ አንገራግረሃል። ምክንያቱም ግልፅና ግልፅ ነበር። ለዓመታት ለብቻህ ተነጥለህ ስታካብተው የነበረው ሃብትና የውስጥ አፈና አሰራርህ የሚጋለጥበት መድረክ በመሆኑ። ተስፋዬ በዚህ « የምርኮኛው ማስታወሻ » ቅንጭብጫቢ መፅሓፍህ የዚህ ኮሚቴ አባላት ስም በተደጋጋሚ የጠቀስክበት ምክንያትም የዚህ ኮሚቴ አባላት የጉሮሮ አጥንት በመሆናቸው መሆኑ አንተንና እነዚያን ሰዎች የሚያውቅ ሁሉ በቀላሉ ሊገነዘበው የሚችል ሀቅ ነው። በዚህ ኮሚቴ ውስጥ ከገባህ በኋላ የመረጥከው አካሄድ ዝምታን ነበር። ዝምታን ለምን እንደመረጥክ የታወቀ ነበር። አንዱ ምክንያት የአቅም ማነስ ችግር ሲሆን ሌላው ሓላርፍ ያለች ጣት የሚለውን አባባል እያስታወስክ ይመስለኛል። ሆኖም ይህ ዝምታ ብዙ አልሄደም። ግልፅ ማንነትህ ፈጦ የወጣው « የቡርቃ ዝምታ » ካሳተምክ በኋላ ነው። ለቡርቃ መፅሓፍ አፃፃፍ ክብሩ አሁንም አለኝ። በይዘቱ ላይ ግን ከፍተኛ ልዩነት እንደነበረን ገልጨልህ የመጀመሪያው የማንነትህ መረጃ ተመዘገበ። ብዙ ሰው እንደሚያውቀው የቡርቃ ዝምታ የኦሮሞን ህዝብ በአማራ ህዝብ ላይ እንዲነሳ ጥሪ ያቀረበ መፅሀፍ ብቻ ሳይሆን የሻዕቢያን አቅም የቆለለና የኢህአዴግን ችሎታ ያንኳሰሰ መፅሀፍ ነበር። በመፅሐፍህ ላይ በተደጋጋሚ ለማሳየት እንደሞከርከው ሻዕቢያ ደርግን የጣለ ብቸኛ ሃይል ነው፣ ያለ ሻዕቢያ ድጋፍ የኢህአዴግ ህልውና አደጋ ላይ እንደነበርና የደርግ እድሜ ሊራዘም ይችል እንደነበር በዚሁ መርዝ መፅሃፍህ በስውርም ይሁን በግልፅ ካስተላለፍካቸው መልክቶች አንዱ ነበር። የመፅሃፍህ ይዘት ባጠቃላይ ሲታይ የአገርህ ልጆች፣ (የድባሩባ) ማለት ሃማሴኖቹ "ነብለሎች" መሆናቸውን የሚሰብክ ይዘት ነበረው። ይህ ይዘት የኦሮሞ ህዝብ በአማራ ህዝብ ላይ እንዲነሳና እርስበርሱ እንዲጨፈጭፍ በሚያውጀው ግልፅ መልክትህ የደበዘዘ ስለነበር በኢህአዴግ ላይ የነበረክህ ንቀትና በሻዕቢያ አይበገሬነት ላይ ተመስርቶ የተፃፈው ጭብጥህ ልብ ብሎ ላላዬ ሰው ብዙ ግልፅ አልነበረም። በኢህአዴግ ሚዲያዎች ኮሚቴ የተነሳው አንዱ ነገር (የመጀመሪያው ጭብጥ እንዳለ ሆኖ) ይኸው ነበር። ስለዚህ የመጀመሪያው ጭብጥ በስፉት ብዙ የተባለበት በመሆኑ በሁለተኛው ጭብጥ ብቻ የተወሰነ ነገር ልበል።

በመፅሓፍህ ላይ እንደገለፅከውና አሁንም ቢሆን በየፓልቶኩ የተኮለኮሉት የዋሆች እንደሚያነበንቡት፤ ሻዕቢያ ኢህአዴግን እየጎተተ አዲስ አበባ እንዳስገባው፤ ካለ ሻዕቢያ ድጋፍ ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሊገባ ይችል

እንዳልነበር ይተርካል። እርግጥ ነው፤ ኢህአዴግና ሻዕቢያ በብዙ መልኮች ተጋግዘዋል። በብዙ መልኮችም ተካክደዋል። ይህ ጉዳይ በጣም ሰፊና የዚህ ፅሑፍ ዓላማም ባለመሆኑ ካንተው ስውር መልዕክት ጋር የተያያዘውን አንድ ዓብይ ጉዳይ ብቻ ላንሳ።

ስለ 80ዎቹ ዓ.ም የህወሓት ድሎች የምታውቀው ይኖር ይሆን?  በወሬ ወሬ የሰማኸው እንደሚኖር በመጠርጠር ወደ ዋናው ቁምነገር ልግባ። በየካቲት ወር 1980 ዓ.ም ዓዲግራት አካባቢ በሚገኘው የምጉላት አምባ የተጀመረው የህወሓት የማጥቃት እርምጃ በአጭር ግዜ ውስጥ ከመቐለ በስተቀር ከሞላጎደል ሁሉንም የትግራይ ከተማዎች ነፃ ያወጣ ኦፕሬሽን ነበር። ይህ ድል ደርግን ብቻ ያስደነገጠ ሳይሆን ሻዕብያን ጭምር ያስገረመ ድል ነበር። ያ የትም አይደርስም የተባለው ህወሓት እነሆ ተአምር ሰራ። ዜናው ከአጥናፍ አጥናፍ ተስተጋባ፤ ሻዕብያ ጆሮም ውስጥ ደረሰ።

እናም አቶ ስብሃት ኤፍሬም .(የአሁኑ የሻዕቢያ ጄኔራል) የሬድዮ መልዕክቱን ለህወሓት ኮማንድ ላከ። ህወሓትና ሻዕቢያ ከ1977 ዓ.ም ድርቅ በኋላ ቀጥተኛ የሆነ ግኑኙነታቸውን አቋርጠዋል። በዛ የሰባ ሰባት ዓመተ ምህረት ድርቅ ደርግ የትግራይን ህዝብ ለማጥፋትና ትግሉን ለማኮላሸት እንደመልካም አጋጣሚ ሲጠቀምበት ሻዕቢያም ወደ ሱዳን የሚሰደደውን ህዝባችን መንገድ ከልክሎ ተመሳሳይ እርምጃ ወሰደበት የሚል በህዝቡም በታጋዩም ልብ ውስጥ የገባ ዘመን የማይሽረው ቂም ነበር። እናም አቶ ስብሃት ኤፍሬም በሬድዮ መልክቱ አቶ ስየ አብርሃን ለማግኝት እንደሚፈልግ መጠየቁ አዲስ ክስተት ነበር። አቶ ስየ አብርሃ ስብሃት ኤፍሬምን ላለማነጋገር ካንዴም ሁለቴ እምቢ ቢልም ስብሃት ኤፍሬም በቀላሉ እጁን አልሰጠም። ስለዚህም አቶ ስየና አቶ ስብሃት ኤፍሬም በሬድዮ ኦፕሬተሮቻቸው አማካኝነት ንግግር ጀመሩ። በወቅቱ አቶ ስየ አክሱም ከተማ ውስጥ ነበር።

«እውነት ነው ደርግን ከትግራይ ከተማዎች ጠራረጋችሁት የሚለው ዜና» ሲል አቶ ስብሃት ጠየቀ። «ምን ጥርጥር አለው! አሁን አክሱም ከተማ ውስጥ ሆኜ ነው እያነጋገርኩህ ያለሁት» ሲል አቶ ስየ መለሰ። አቶ ስብሃት አድናቆቱንና ግርምቱን ገልፆ ህወሓትና ሻዕቢያ እንደገና ለምን ግንኙነታቸውን አያድሱም

የሚል ጥሪ አቀረበ። ከ1977 ዓ.ም ኩርፊያና ቂም በኃላ ህወሓትና ሻዕቢያ እንዴት ግንኙነታቸውን አደሱ? የሚለውና በብዙ የታሪክ ፀሓፊዎች፣ የሁለቱም ድርጅቶች ታጋዮችም ጭምር የሚጠይቁት ጥያቄ አለ። መልሱ ይኸው ነው። ከ80 ዎቹ የህወሓት ድሎች በኃላ በሻዕቢያ አነሳሽነት፤ በአቶ ስብሃት ኤፍሬም በኩል ጥሪ ቀረበ። በወቅቱ አቶ ስየና አቶ ስብሃት ኤፍሬም ባደረጉት የሬድዮ ግኑኚነት የትብብሩን ዝርዝር ለመነጋገር የማይቻል ስለነበር አቶ ስብሃት ኤፍሬም በዝርዝር ጉዳዩ ላይ ለመነጋገር ሱዳን ውስጥ በአመራር ደረጃ ለመገናኘት ሀሳብ ሲያቀርብ አቶ ስየም ከሌላው የህወሓት አመራር ጋር ተነጋግሮ መልስ እንደሚሰጥ ቃል ገብቶ የሬድዮ ግንኙነቱ ተቋረጠ።

የህወሓት አመራር ጉዳዩ ላይ ተነጋገረበት። የሻዕቢያና የህወሓት ግኑኚነት መታደስ የደርግን ዕድሜ የሚያሳጥር መሆኑ ታምኖበት ግኑኚነቱ እንዲታደስ ተወስኖ አቶ ስየና አቶ መለስ ከሻዕብያ መልዕክተኛ ጋር ሱዳን ውሰጥ እንዲገናኙና በግንኙነቱ መታደስ ዙሪያ እንዲነጋገሩ ስልጣን ሰጥቶ ተበተነ። እና የፕሮፖጋንዳ ሰራተኞችም ከዛ በፊት በሻዕብያ ላይ ስታነጣጥር የነበረችው ብዕራቸውን ወደ አፎቷ እንዲመልስዋት ተነገረ። ከዚ በኃላ ምን ሆነ መሰለህ ተስፋዬ ሻዕቢያ የዋዛ ድርጅት አይደለም። ህወሓት እነዚያን ድሎች አፈሶ፤ በድል አድራጊነት መንፈስ ታጅቦ ግንኙነት ለማድረግ አልፈለገም። እና ከግንኙነቱ በፊት አንድ መንፈስ የሚዘራ ስራም መስራት እንዳለበት አሰበ። የወቅቱን የወታደራዊ ሚዛን ገመገመ። ደርግ ትግራይ ውስጥ በደረሰበት ሞት በከፍተኛ ደረጃ መዳከሙን አየ እናም በመጋቢት ወር 1980 ዓ.ም አፍዓበት .( ኤርትራ ውስጥ) በናደው እዝ ላይ የማጥቃት እርምጃ ሰንዝሮ በለስ ቀናው። ደርግ ትግራይ ውስጥ ከደረሰበት ሽንፈት ሳያገግም የተሰነዘረበት የማጥቃት እርምጃ በመሆኑ በቀላሉ ተፈረካከሰ። ሻዕቢያ ትግራይ ውስጥ ህወሓት ባስመዘገበው ድል ታጅቦ ናዳውን ናደው ብቻ ሳይሆን ለመጀመርያ ግዜ ከተደበቀበት ከናቅፋ ተራሮች ላይ መውረድ ጀመረ። አባባሌ ግልፅ ከሆነ የናደው ዕዝ ሽንፈት ምንጩ፡ የሻዕቢያ ጥንካሬ ብቻ ሳይሆን ደርግ ትግራይ ውስጥ 1980 ዓ.ም በደረሰበት ሽንፈትም ጭምር ነው።

ከዚያ በኃላ ምን ሆነ መስለህ ተስፋዬ። ቅንጭብጫቢ ታሪክ አይደለም እየነገርኩ ያለሁት። ልብ ብልህ ካዳመጥክ ይህም ለሌላ ቅንጭብጫቢ ፅሑፍ መንደርደሪያ

ሆኖ ሊያገለግልህ ስለሚችል በጽሞና ተከታተል። ህወሓትና ሻዕቢያ ግንኙነታውቸውን ለማሳደስ ሱዳን ውስጥ ሲገናኙ የዚህ ግንኙነት ማብሰርያና ማጠናከርያ የተቀናጀ ወታደራዊ ኦፕሬሽን ለማድረግ ተስማሙ ።

መቼም የወሬ ወሬ ጣምራ ክንዳችን የሚለውን ዘመቻ ሰምተህ ይሆናል። ከዓላጀ ተራራ እስከ ግራት ካሕሱ አላማጣ ከተማ ድረስ የመሸገውን የደርግ ሰራዊት የጠራረገው ዘመቻ። የዘመቻው መጠሪያ ጣምራ ክንዳችን ሲሆን እንደ አንተ ዓይነቱ ባይተዋር የዘመቻው ስም ጣምራ ክንዳችን የሆነው ህወሓትና ብአዴን የያኔው (ኢህዴን) በጋራ ያካሄዱት ዘመቻ ስለሆነ ነው የሚል ድምዳሜ አላቸው። በወቅቱ ይህንን ቁም ነገር ለማሰጨበጥ የድርጅቱ ጋዜጠኞች ብዙ መጻፋቸውን አስታውሳለሁ። ህወሓትና ኢህዴን በጋራ ወታደራዊ ኦፕሬሽን አካሄዱ፣ የጋራ ግንባር (በኋላ ላይ ኢህአዴግ) የሆነው የሚፈጠርበትንም መሰረት ጣሉ ብለው ፅፈዋል።

ሓቁ ግን እንደዛ እንዳይመስል፣ ነገሩ ወዲህ ነው። ህወሓትና ሻዕቢያ ሱዳን ውስጥ ግንኙነቱን ሲያድሱ ከደረሱበት ስምምነት አንዱ የተቀናጀ ወታደራዊ ዘመቻ በማካሄድ የደርግን እድሜ ማሳጠር የሚል ነበር። ስለሆነም የዘመቻው ቀን ተወሰኖ ህወሓት ትግራይ ውስጥ ደርግን የመደምሰስ ተልዕኮ እንዲወጣ ሻዕቢያ ደግሞ በዚያው እለት ተመሳሳይ እርምጃ በኤርትራ ውሰጥ እንዲያከናውን፣ ደርግ በሁለቱም ግንባር የተከፈተበትን የተቀናጀ ዘመቻ መቋቋም አቅቶት በአጭር ግዜ ውስጥ እጁን እንዲሰጥ ማድረግ ሆኖ የዘመቻውም ስም «ጣምራ ክንዳችን» በትግርኛ ደግሞ «ስሙር ቅልፅም» እንዲሆን ተስማምተው ነበር።

ተስፋዬ! ሻዕብያ የዋህ አይደለም። ደርግ በሁለቱም ግንባር ከደረሰበት ሽንፈት ለማምለጥ ያለ የሌለ ሃይሉን ማሰባሰብ ጀምሮ ነበር። በተለይ ትግራይ ውስጥ የደረሰበት ሽንፈት በኤርትራና በመሃል አገር ያለውን የሰራዊት ትስስር የሚበጥስና ኃይሉን እንዳያቀናጅ የሚያደርገው በመሆኑ ከኤርትራ ይልቅ ትግራይ ውስጥ ያለው የህወሓት ኃይል መደምሰስና የኤርትራንና መሃል አገር ግንኙነት መስመር ማስቀጠል ዋነኛ ዝግጅቱ መሆኑን ሻዕቢያ አውቆ ነበር።

ህወሓትም የዋዛ አይደለም። ተመክሮ የሻዕቢያን የክህደት ታሪክ አስተምሮታልና ሻዕቢያ በተቆረጠው ቀን ውግያ ካልጀመረ ምን ሊሆን ይችላል? ለሚለው ጥያቄ መልስ ማዘጋጀት ነበረበት። ስለሆነም በዚያ ዘመቻ ወቅት የኢህዴን ታጋዮች ከአላጀ እስከ ግራት ካሕሱ በተደረገው ዘመቻ (ትግራይ ውስጥ ያደረጉት ትልቁ የጋራ ዘመቻ ነው) እንዲሳተፉ ተደረገና ምናልባት ሻዕቢያ ቃሉን ካልጠበቀ የዘመቻው መጠሪያ የህወሓትና የኢህዴን ጣምራ ክንድ ያካሄደው ኦፕሬሽን ነው የሚል መልስ አዘጋጅቶ ወደ ጦርነቱ ገባ። ይህ ዘመቻ ተጀምሮ ድሎች መታፈስ ሲጀምሩና ዜናው ሲደርስ ቶሎ አልተዘገበም። ምናልባት ሻዕቢያም ተመሳሳይ ዘመቻ ያደርግ ይሆናልና ዜናውን ከሻዕቢያ ድል ጋር በማስተሳሰር ስለሚሰራ ጠብቁ የሚል ትዕዛዝ በወቅቱ ለድምፂ ወያነ ትግራይ ጋዜጤኞች ተላልፎ ነበር። ምን ይሄ ብቻ ሻዕቢያን የሚያወድስ ግጥም እንዲፃፍም ታዟል፣ ጋዜጠኞች የሻዕቢያን ሬድዮ ከፍተው ቀኑን ሙሉ ቢጠብቁም የሻዕብያ ነገር የውሃ ሽታ ሆኖ በመቅረቱ፣ የህወሓትንና የኢህዴንን ጥምረት በሚያሳይ መልኩ ዜናው፣ ግጥሙና ኃተታው ተፅፎ መቅረቡ እኔው ራሴ ህያው ምስክር ነኝ።

አዎ! ሻዕቢያ ምክንያት ነበረው። ደርግ በህወሓት የደረሰበትን ሽንፈት ለመበቀል ያላደረገው ዝግጅት እንዳልነበረ አውቋል። ነብሰ በላው ለገሰ አስፋው የትግራይ ራስ ገዝ ባለሙሉ ስልጣን ሆኖ መመደቡ፣ የህወሓትን ዓቅም ለመስበር አስፈላጊ የተባለ ዝግጅት መደረጉ፣ ወታደር የሰላ ሳንጃና ድቁስ ተሰጥቶት የበጎችና ፍየሎች ሆድ እየቀደደ እርጥብ ጉበት እየበላ እንዲዘምት መታዘዙ፣ የትግራይ አርሶ አደር ቤቶችን ለማቃጠል ክብሪት ተሰጥቶ ለመዝመት መዘጋጀቱ በስፋት ታውቋል። (ለመሆኑ ተስፋዬ አንተ ወደ ደብረታቦር ስትዘምት ምን አይነት ድቁስ ነበር የተሰጠህ? ቂ… ቂ… ቂ…) ዓልዓሳን ታውቀዋለህ? ዓልዓሳ ተምቤን ውስጥ የሚገኝ መንደር ነው። እዚያ መንደር ውስጥ በአንድ ጀንበር የተቃጠሉትን 700 የአርሶ አደር ቤቶችን አታውቃቸውም። ከሳምረ እስከ ዓድዋ ዓንዶ፣ ገለበጻ ድረስ በቁማቸው ጉበታቸው እየተበጠበጡ የተገደሉትን በጎችና ፍየሎች ላንተ የሌሉ ታሪኮች ናቸው። የሰው ልጅና የአህያ ስጋ አንድ ላይ የተፈተበቱበት ሃውዜን ተረት ተረት ሊሆን ምን ቀረው? አዎ ደርግ ይህን ያደረገው ያኔ ነው። ሻዕቢያም በዚያን ወቅት ለምን ዘመቻውን አላካሄደም የሚለው ያልተመለሰ ጥያቄ ቢሆንም በተለመደው ክህደቱ

ህወሓትንና የትግራይ ህዝብን ለከፍተኛ ጥቃት እንዲጋለጡ በር መክፈቱ ነበር። ያም ሆነ ይህ ዋነኛው ተጠያቂ ግን አንተን ለምርኮና ለዚህ ስም ያበቃህ የደርግ ስርዓት ነበር።

ህወሓት ኢህአዴግ ከዚህ በኋላም ቢሆን አንድ የፀና ዓላማ ነበረው። ይህ የትግራይን ህዝብ ነጥሎ በአዋጅ «ትግሬ ገዳይ» እየፎከረ ያለውን የደርግ ስርዓት መደምሰስ የሚቻለው በተቀናጀ ትግል ነው የሚል ዓላማ። ሻዕቢያ በወቅቱ ዘመቻውን ያላካሄደው በታወቀው ክህደቱ ቢሆንም ህወሓት ይህንን እያወቀ ግንኙነቱ ሳይቋረጥ መቀጠልን መርጦ አፋፍ ላይ የነበረውን ደርግ ማስወገድ። በዚህም መንፈስ ወደ 81 ዓ.ም ዘመቻም ተሸጋገረ።

እዚህ ላይ ለማለት የምፈልገው ብዙ ሰዎች ስለሚደናገሩበት ጉዳይ ነው። ስማ ተስፋዬ ደርግ የተሸነፈው ግንቦት 83 ዓ.ም አይደለም። ብዙ ሰዎች እንደሚሉት ናደው ዕዝ ከተመታ በኋላም አይደለም። ወይም ስሞኑን በሻዕቢያ ቴሌቪዥን እንደምናየው ከምፅዋ ጦርነት በኋላም አይደለም። ደርግ የተሸነፈው ተካ ተስፋይ፣ ሳምረ ፣ ዓንዶ ገለበዳ፣ አለቃህ ጄኔራል አበበ ሃይለ ስላሴ የነበረበት ዳንሻ ወዘተ. እየተከታተፈ ከከረመ በኋላ ሽሬ ላይ በዳግማዊ ሃውዜን ዘመቻ አማካኝነት ድባቅ ተመታ። በሌላ አባባል ደርግ የተሸነፈው አንተ በደርግ ወታደራዊ ስልጠና ውስጥ እያለህ ትግራይ ከደርግ መንጋጋ ነፃ ስትወጣ ነው። በለገሰ አስፋው አዝማችነት እንደገና ተጠናክሮ የመጣው የደርግ ሰራዊት ሽሬ ላይ ተመታ፣ አይሆኑት ሆኖ ተፈረካከሰ፣ ትግራይ ነፃ ወጣች፣ ደርግ እንዴ ኤርትራ ላይ ሲመታ ከትግራይ ጦሩን ልኮ ማገዝ፣ ትግራይ ላይ ሲመታ ደግሞ ከኤርትራ ጦሩን አንቀሳቅሶ የትግራይን እንቅስቃሴ መግታት የሚችልበት ሁኔታ ተቋረጠ። እናም ያኔ ደርግ ተሸነፈ። ከዚያ በኋላ የነበረው ስራ እንዳንተ ዓይነቱን አዲስ ጄሌ የመቃረም ስራ ነበር። የጉናም ሆነ የሌሎች ግንባሮች ውግያ ጠንካሮች ነበሩ ሲባል ከደርግ ጥንካሬ የመጡ ጥንካሬዎች እንዳይመስሉህ። ነገሩ ወዲህ ስለሆነ እሱን ልዝለለው።

ሌላው ተረት ተረት የሽሬ ጦርነት (የዳግማዊ ሃውዜን ዘመቻ) በሻዕቢያ መካናይዝድ ብርታት የተገኘ ድል አድርገው የሚያቀርቡ ተረተኞችም አሉ። አንተም ጭምር በቡርቃ ዝምታ መርዛማው መፅሀፍህ። እርግጥ ነው በሽሬ

ጦርነት የሻዕቢያ መካናይዝድ ጦር እንደነበር አይካድም። ጦርነቱ የተካሄደው ግን በመከናይዝድ ጦር አልነበረም። «ታባ ወያናይ ፅንዓትን » ታውቀዋለህ? ፈርዶብህ! አታውቀውም አይደል? ይህም ቦታ አንተ እዚያው ደርግ ማሰልጠኛ ጣቢያ ውስጥ  የቆርቆሮ ቲማቲም ስትለቃቅም ጀግኖች ከፍተኛ መስዋእትነት የከፈሉበት ቦታ ነው። በአንድ በኩል ታንክ (በደርግ)፣ በሌላ በኩል ክላሽንኮቭ ( በኢህአዴግ) የተፋለሙበት የውግያ ቦታ ነው። ገና ጦርነቱ ሳይጀመር፣ ገና ጎህ ሳይቀድ የደርግና የኢህአዴግ ሰራዊት የተቃለቀሉበት፣ መካናይዝድ ጦርም ይሁን የአውሮፕላን ድጋፍ በጦርነቱ ውስጥ  እድል እንዳያገኝ የተከለከለበት፣ አውሮፕላንም ይሁን መካናይዝድ ጦር ከተኮሰ ሁሉንም የጦርነት ተሳታፊዎች በጅምላ የሚጨፈጭበት፣ በመሆኑ ደርግም ይሁን ኢህአዴግ የመካናይዝድና የኦውሮፕላን ድጋፍ ሳያደርጉ እግረኛ ሰራዊት ተቀላቅሎ የተፋለመበት ጦርነት ለመሆኑ በወቅቱ በጦርነቱ የተሳተፉ የደርግ ወታደሮችም በገሃድ የሚያውቁት ጦርነት ነው። ስለዚህ ጦርነቱ እነዚያ ድንቅ የህዝብ ልጆች ታንክን በክላሽን ኮቭ የማረኩበት፣ ወይም እያሱ በርህ አጫውቶህ ከሆነ አርሶ አደሩ እንደ አንተ ዓይነቱ የደርግ መኮንን በድንጋይ የማረከበት ወቅት በመሆኑ የሻዕቢያ መካናይዝድ ፋይዳ ያለው ድጋፍ አላደረገም። ይህንን ማረጋገጥ ከፈለግክ በወቅቱ የሻዕቢያ የመካናይዝድ ሃላፊ ሆኖ ሽሬ ላይ የዋለውን አጎትህን ወዲ በርህን ጠይቀው፣ (ወዲ በርህ ከኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በፊት በኤርትራ ኤምባሲ የወታደራዊ አታሼ ሃላፊ ነበረ ሰው ነው)። የወሬ ወሬ ሰምተህ እንደሆነ አላውቅም። ሽሬ ከተማ አካባቢ የሚገኘው አምባ ከዚያን ውግያ በኋላ «ታባ ወያናይ ፅንዓት» (የታጋይ ፅናት የተመሰከረበት አምባ) ተብሎ ተሰየመ።

በኔም ይሁን በብዙ ታጋዮች እምነት የዳግማይ ሓውዜን ኦፕሬሽን (የሽሬው ጦርነት) የደርግና የኢህአዴግ የኃይል ሚዛን የተገለበጠበት ሳይሆን የደርግ ውድቀት ፍፁም ፍንቱው ብሎ እንዲታይ ያደረገ ጦርነት ነበር። የሃይል ሚዛኑ የተገለበጠው ከ80 ዎቹ የኢህአዴግ ማጥቃት እርምጃዎች ማለትም ከመቐለ ከተማ በስተቀር ሁሉም የትግራይ ከተማዎች ነፃ ከወጡበት ጊዜ በኋላ ነው። ለነገሩ እንደዚህ ዓይነቱ ትልቅና ታሪካዊ ቁም ነገር ቅንጭብጫቢ ወሬ ለሚለቅም ምርኮኛ ምኑም ስላልሆነ እንደዚሁ ልዝለለው። የዳግማዊ ሓውዜን ኦፕሬሽን በደርግ ውድቀት የነበረው ወሳኝ ሚና ተዘንግቶ ደርግ የወደቀው ከዚያ በኋላ በተደረጉት ጦርነቶች ወይም ደግሞ ሻዕቢያ ኤርትራ ውስጥ  ባደረጋቸው

ዘመቻዎች አማካኝነት እንደሆነ አድርገው የሚያቀርቡ ድርሳኖችን በጭፍን ሳይሆን በማስረጃ እቃወማቸዋለሁ።

አየህ ምን መሰለህ፣ ደርግ መሃል አገር የነበረውን ሰራዊት የትግራይ ምድርን አቆራርጦ ኤርትራ ውስጥ ሊያስገባ የሚችልበት ዕድል ያጣው 80 ዓ.ም ትግራይ ውስጥ በተደረገው ዘመቻ እና በሽሬ ጦርነት ምክንያት ከትግራይ ተጠራርጎ በመውጣቱ ነው። ኢህአዴግ ከዚያ በኋላ ያደረጋቸው የመሃል አገር ዘመቻዎች፣ አንተ የተማረክበት የደብረታቦር ውግያም ጭምር፣ ቀላል የሆኑት ደርግ ከኤርትራ መሬት ረዳት ጦር የሚያንቀሳቅስበት ከሽሬ ጦርነት በኋላ በማክተሙ ነው።

ከቡርቃ ዝምታ ሕትመት በኋላ የነበረው ያንተ የማንነት ማስረጃ ከዚህ ይመነጫል። መፅሓፉ ብዙ አወዛጋቢና ከፋፋይ ይዘቶች የነበሩት ሲሆን በኢህአዴግ ልሳኖች ስብሰባ ላይ የቀረበብህ ሂስ የኦሮሞ ህዝብ የሌለበትን ስነ ልቦና ፅፈሃል፣ በህዝቦች መካከል ጥልና መቃቃር እንዲፈጠር አድርገሃል አሁን እየተመሰረተ ላለው የህዝቦች አንድነት ስርዓት ጋሬጣ አስቀምጠሃል፣ የሚለው አንዱ ትልቁ ጉዳይ ነበር። ከዚህ ጋር በሁለተኛ ደረጃ የቀረበብህ ሂስ የሻዕቢያን ድል አድራጊነት በየትኞቹ የገድል መፃህፍት ነው ያነበብከው? ለመሆኑ በሻዕቢያ ተጨባጭ አቅም ላይ ያለህ ግንዛቤ ምንድን ነው? በዚህ መፅሀፍ ላይ ያነሳኸው ጭብጥ መነሻው ምንድን ነው የሚል ነበር:: ከዚህም በመነሳት ትልቅ የታሪክ ስህተት ፈጥረሃል የሚል ሂስ ቀርቦብሃል። ኢህአዴግ ታግሎ ያመጣውን ድል በምን ሂሳብ ነው ለሻዕቢያ አሳልፈህ የሰጠኸው? ይህን መረጃ ከየት አመጣኸው? የሚልም ጥያቄ ቀርቦብሃል። እንዳመልህ መልስ አጥሮህ አይኖችህ ሲቁለጨለጩ አሁንም ይታየኛል። አሁን ገና ለገና የምትገመገምበት፣ ምስክር አቅርብ የማትልበት አገር ሄድኩኝ ተብሎ ታሪክ ቢጣመም እውነታውን አይቀይረውም። ይህን ርእሰ ጉዳይ ዝርዝር አድርጌ ለመፃፍ የተገደድኩት ላንተ አለባልታ የሚመጥን መልስ ነው የሚል እምነት ኖሮኝ አይደለም። ሆኖም ሻዕቢያ ኢህአዴግን እየጎተተ አ/አበባ አስገባው የሚሉት ቧልተኞች የሚቀባጥሩትን አፍ ለማዘጋትና፣ በተቃራኒው ጎራ የተሰለፉት የኢህአዴግ ወዳጆች በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ምላሽ አጥሯቸው የሚቸገሩበትን ሁኔታ በመቅረፍ ተጨባጭ መልስ እንዲኖራቸው ለማገዝም ጭምር ነው።

አንተና አቶ በረከት ያደረጋችሁት ክርክር በቦታው ባለመኖሬ እንደዚህ ነበር ባልልም፣ የቡርቃ ዝምታ ሻዕቢያንና ብአዴንን ወይም ሻዕቢያንና ህወሓትን እያነፃፀረ የሚተርክ ሳይሆን ሻዕቢያንና ኢህአዴግን እያነፃፀረ የሚተርክ በመሆኑ አቶ በረከት ለምን የብአዴንን ሚና አሳነስከው ወይም አላጎላኸውም በሚል የሚከራከርህ አይመስለኝም። ካገር የወጣህበትን ምክንያት ፓለቲካዊ ይዘት እንዳለው አስመስለህ ለማቅረብ ከተጠቀምክባቸው ነጥቦች አንዱ ለመሆኑ ስለማያጠራጥር በኋላ እመለስበታለሁ። ዋናው ቁምነገር ግን አቶ በረከት እንደዚያ ዓይነት ጅላጅል ክርክር እንደማይከራከር እኔና አንተ ብቻ ሳንሆን የግንቦት 7 አለቆችህም ጥርት አድርገው ያውቁታል። ከጠረጠርክ ጠይቃቸው። ይህን የሚመለከት ግምገማ ጢት ተጀምሮ እንደልማድህ ማሪዋና ወደ ምትምግበት ደብረዘይት ከሰዓት በኋላ ጠፍተህ የሄድከውም በመጨረሻ ላይ ሊደረስበት የሚቻለውን ድምዳሜ ሰግተህ እንደሆነ ግልፅ ነበር:: አንተ ያታለልክ መስሎህ ሊሆን ይችላል እንጂ የት እንደሄድክ ተደርሶበት ነበር። ስለዚህ ተስፋዬ ይህ እንግዲህ የመጀመሪያው የፓለቲካዊ ማንነትህ መገለጫ ተብሎ ይመዝገብ።

ተስፋዬ ስለ ወይን ጋዜጣ ያለህ ግንዛቤ ምን ያህል ነው? ብርቅየ የህዝብ ልጆችን ያታገለ፣ አንተ መጀመሪያ የተቀላቀልክበትና አሁን ለመቀላቀል ማመልከቻ እያስገባህበት ያለውን የትምክሕተኞች ጎራ ሲያጋልጥ የዘለቀ የታጋይ ህዝቦች ልሳን ነው። ወይን ማለት እፎይታ እንዳይመስልህ።

ወይን ከትጥቅ ትግሉ ማክተም በኋላ ነጥሮ የሚታወቅባቸው ዓምዶች አሉት። ያ በቅንጭብጫቢ ማስታወሻህ ያሾፍክበት አታኽልቲ ከቀረፃቸው ዓምዶች አንዱ ዓምድ «ተጋድሎ» ነው። አሁንም ድረስ ዓምዱ አለ። ተጋድሎ የሚለው ዓምድና ወይን አንድም ሁለትም ናቸው። የማይነጣጠሉ። ታድያ አንተው ደፋር ሆንክና የጋዜጣው የአምድ ስም ሰርቀህ ተጋድሎ የሚል መፅሓፍ አሳተምክ። የልሳን ዓምድ ያለፍቃድ መውሰድ አግባብ አይደለም፣ አንድ ማስፈቀድ ነበረብህ፤ ከዚያም በላይ የመፅሓፍህን ርእስ ከወይን ጋዜጣ የወሰድከው መሆኑን መግለፅ ነበረብህ ተብለህ ነበር የተነቀፍከው:: አንተ ግን አሁን በዚህ የምርኮኛ ኑዛዜህ አታኽልቲ ርእሱን መፅሓፍ ላሳትምበት አስቤ ነበር ብሎ ተቆጣ ብለህ ስትቀላምድ ገረመኝ። ዓምዱን እኮ ለጋዜጣው የቀረፀው እሱ እራሱ አታኽልቲ

ነው። እሱ ለወለደው የጋዜጣ ዓምድ ስም ገና ለሚደርሰው የመፅሓፍ ስም ሊጠቀምምበት የሚዳዳው በምን ሂሳብ ነው? ውሸትም እኮ ትንሽ ገደብ አለው። አታኽልቲ መፅሓፍ ለመፃፍ ፈልጎ ርእስ ሲያጣ ቂ...ቂ...ቂ...። ያም ሆኖ ይህ ግን በምርኮ ኑዛዜህ የዘባረቅከው ምን ማለት እንደሆነ ይኸው እውነታ የሚያጋልጠው ይመስለኛል።

ተስፋዬ ሌላው ችግርህና በየወቅቱ የተነገረህ ጉዳይ መነሻ ሃሳቦችን የመስረቅ ሱስ ነው። ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ የሚባሉትን ቅፆች የሚያውቅ ሰው ወደኋላ ይመልከት። በተለይ ትግርኛ የሚያነብና ወይን ጋዜጣን በቅርብ የሚያውቅ ሰው በዚያ ቅፅ የተካተቱትን ይዘቶች እንዲያስታውስ ልጋብዝ። አብዛኛዎቹ አንተ የፃፍካቸው ፅሑፎች መነሻቸው ወይን ጋዜጣ መሆኑን ሸምጥጠህ እንደምትክድ ቢታወቅም ወይንና እፎይታን ያነበበ ሰው ሓቁን ይገነዘበዋል። የወይን ጋዜጠኞች የደከሙበትን ስራ የተወሰነ ቅንጭብጫቢ ማስዋብያ እየጨመርክ ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ የሚል ኢምፓየር ፈጠርክና ኪስህን አደልበህ ፕሪቶሪያ ላይ የኢንተርኔት ኢምፓር ከፈትክበት።

ይህ ብዙ ጊዜ በወይን ጋዜጠኞች ቅሬታ እየፈጠረ የቆየ ጉዳይ ቢሆንም ችላ ተብሎ ለብዙ ጊዜ ቆየ። አንድ ጊዜ ግን የንቀትህ ንቀት የሙሴን ታሪክ ስታዘጋጅ ዋነኛው ይዘት የወይን ጋዜጣ ዝግጅት ሆኖ እያለ የላቀ ምስጋናውን ለሻዕቢያ መፅሔቶች ለነ ሕድሪና ሓዳስ ኤርትራ በመስጠትህ አሁንስ ገደብ አለፍክ ተብለህ ተነቀፍክ። ሓሳብ መውሰዱን ውሰድ ለምን ተገቢውን ክብርና የወሰድክበትን ምንጭ አትጠቅስም የሚል ነቀፌታ ቀረበብህ።

ሌላው ስለአቶ ሱሌማን ደደፎ የዘባረቀከው ጉዳይ እጅጉን ገርሞኛል። ስለ አቶ ሱሌማን የፃፍከው አዎንታዊ ችሎታ እኔም እጋራዋለው። አቶ ሱሌማን እዚ በመድረሱም እደሰትበታለሁ። ሹመት ያዳብር ብቻ ሳይሆን ይገባዋልም ባይ ነኝ።

ሆኖም አንድ በጣም የገረመኝ ነገር በመፃፍህ መልስ ሳልሰጥበት ማለፉን አልፈቀድኩም። አየህ ተስፋዬ አንተ ሁሌም የበታችነት ስሜት ሲጫወትብህ

የነበርክ ሰው ነህ። ታስታውስ እንደሆነ ኢህአዴግ አ/አበባ ሲገባ በመንግስት ሚዲያዎች እንዲሰሩ ከተመደቡት ጋዜጠኞች መካከል አንዱና ታታሪው አቶ ሱሌማን ነበር:: በስልጣን ግን አንተ የፕሬስ መምሪያ ሀላፊ ሳለህ አቶ ሱሌማን ደግሞ የሬድዮ ፕሮግራሞች ኃላፊ በመሆኑ አንተ የበላይ እሱ የበታች ሆናችሁ በችሎታ ግን የትየለሌ ነበራችሁ። ይህ እንቅልፍ ነሳህ። እናም ልትቀብረው አሰብክ:: ማን ጋር ሄደህ እንዳሳበቅክ ባላውቅም አቶ ሱሌማን ከተወለደበት ቦረና አካባቢ (ለነገሩ አቶ ሱሌማን የቦረና ሰው እንጂ አንተ እንደቀላመድከው የአርሲ ልጅ አይደለም) ካመጣት ባለቤቱና ልጆቹ ጋር ያለምንም ገቢ እንዲጣሉ አደረክ።

ይህ በሆነ በወሩ ነበር አቶ ሱሌማን እኔ ጋር የመጣው። የደረሰበትን ችግር ገለፀልኝ። እቤቱ ድረስ ሄጄ ያለበትን ሁኔታ በአይኔ በብረቱ አይቼ አዝኛለሁ። ይህንን ካየሁ በኋላ ዝም ያልኩሁ እንዳይመስልህ። እንዳንተ አይነት ጨካኝ የፈፀመውን ድርጊት ፊት ለፊት መመከት በወቅቱ አቅሙ ባይፈቅድልኝም አቶ ሱሌማንን ወደ ድርጅቱ የመመለስ ጉዳይ ግን እንደ አንድ የተቀደሰ ተግባር ነበረ ያየሁት። እናም የት ሄድኩ መሰለህ? አቶ በረከት ቢሮ። የሆነውንና ያየሁትን በሙሉ ለአቶ በረከት ነገርኩት። እሱም አዘነ። አንድ ውሳኔ እንደሚወስን ነግሮኝ ተለያየን። ይህንን ለአቶ ሱሌማን ነገርኩት። በሳምንቱም አቶ ሱሌማን ሬድዮ ፋና ተመድቦ መስራት ጀመረ።

አቶ ተስፋዬ ይህን ታሪክ ገለበጥከው። አቶ ሱሌማን ወደ ስራ የመለሰው አቶ በረከት ሆኖ እያለ፣ አቶ በረከት ሱሌማንን እንዳባርር ተማለደኝ ትላለህ? የአቶ ሱሌማን መባረር አቶ በረከት ካመነበት ለምንድነው አንተን የሚለማመጠው። ውሃ ወደ ላይ ይፈሳል እንዴ? አንተ ነህ የነበርከው አለቃው ወይስ አቶ በረከት? አስቂኝ። እዚህ ላይ አቶ ሱሌማን ሀቁን ይነግርህ ይሆናል። አቶ በረከትም እንደዚሁ። ሃቁ ግን አንተ እኔ በወቅቱ ባላወቅኩት ሰው ወሻክተህ አቶ ሱሌማንን እንዳመልህ በረንዳ ላይ ልትጥለው አሴርክበት፣ ለተወሰነ ወራት አንከራተትከው። እኔም አቶ በረከትን ተማፅኜ ወደ ስራው ተመለሰ። ግን ደፋር ተናዛዥ ነህና አቶ በረከት አቶ ሱሌማንን እንዳባረር ተማፀነኝ ትላለህ:: “ዘመንያ ግርምቢጥስ ማይ ንዓቐብ”! ይባል የለ::

## ግን ለምን ከአገር ወጣህ?

ባለ ጉዛዜው ለመሆኑ ካገር የወጣህበትን ምክንያት ከአቶ በረከትና ከአቶ ክንፈ ጋር ለማያያዝ የሞከርክበት ምክንያት አምነህበት ነው? የምሬን ነው። አንድ ግዜ አቶ መለስ ያለውን ነገር አስታወስከኝ። አቶ መለስ ስለምን ተጠይቆ እንደተናገረው ባላስታውሰውም « አሜሪካ እጁ ረጅምም ሰፊም ነው » ያለውን ግን ሁሌም አስታውሸ እስቃለሁ። አንዳንዴም እንዳንተ አይነቱ ውሸታም ሲያጋጥመኝ እጠቀምበታለው።

ምን ማለቱ መሰለህ? አሜሪካ እጁ ሰፊ ስለሆነ አንዴ በጥፊ ከመረገብህ ትወድቃለህ፣ እረጅም በመሆኑም ቶራቦራ ብትገባም ይደርስብሃል ማለቱ ነበር። እናም አቶ በረከትና አቶ ክነፈ አንተን የሻዕቢያ ሰላይ ነው ብለው የሚጠረጥሩህ ከሆነ አንተን አንጠልጥሎ የሚገባህን ቅጣት ለመስጠት ረጅምና ሰፊ እጅ አላቸው፣ ነበራቸው:: ለመሆኑ ይህን በማለት ማን ያምነኛል ብለህ ነው? ከነ አቶ በረከትና ከነአቶ ክንፈ በላይ እኔን ከለላ የሰጠኝ ሌላ ሰው ነበር ብለህ አልነገርከንም:: ቢኖርም ተስፋዬ የሚባል አንድ ምርኮኛ የሻዕብያ ሰላይ ሆኖ ተገኘ ወይም የኢህአዴግ ፀር መሆኑ ተረጋገጠ ብሎ የደህንነት ሹሙ ካመነበት ይህንን እምነት ማነው የሚጥሰው? “ጅብ የማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ” አለ ይባል የለ እና አንተም ይህን ጅላግል አባባል ይዘህ ግንቦት 7 በር ላይ ትልቅ ሰው ለመሆን እየሞከርክ ነው::

ነገሩ ወዲህ ነው ተስፋዬ። ታስታውስ እንደሆነ በመጨረሻዎቹ ያንተ የሽሽት ቀናት የግምገማ አጀንዳዎች ዋነኛው ጭብጥ ያንተ የንግድ ኢምፓየር የሚመለከት መሆኑ እየተከሰተልህ መጥቶ ነበር። ለመሆኑ በፋና ዲሞክራሲ ስም የሚወጡት መፃህፍት በድርጅት ገንዘብ እየታተሙ ገቢያቸው ለማን እየዋለ ነው? የሚለው ጉዳይ ግንባር ቀደም አጀንዳ እየሆነ መጣ። ሂሳባችሁን ኦዲት እንድታስደርጉም በኢህአዴግ የፋይናንስ ቢሮ በኩል በነ አቶ ሕቡር፣ ጫናው በረታ። በመሃሉ የህወሓት ኢህአዴግ አመራር በወቅቱ በተፈጠረው ክፍፍል በውስጡ ሲታመስ የሰው ቀልብ እዚያ ጋ መጠመዱን አይተህ፣ የፋና ዲሞክራሲ ሰራተኞች ደሞዝ ሳትከፍል፣ ኢምፓየርህ ለህትመት ተበድሮት የነበረውን ገንዘብ ሳታወራርድ፣ የነ አቶ እሸቱን ፕሮቪደንት ፈንድ ሳይቀር ይዘህ ኬንያ ላይ

ታየህ። በዚያ ገንዘብ ኬንያ ውስጥ በጎበኘሃቸው የምሽት ክበቦች እየጨፈርክ፣ እንደ አባባልህ በየኬላው ዶላር እየበተንክ ፕሪቶሪያ ገባህና ቱጃር ነጋዴ ሆንክ። አሁንማ ነገርከን፣ እንዲያውም ድባሩባ(ኤርትራ) ሄደህ ለገጠር ዘመዶችህ ማቋቋሚያ ድርጅት ከፍተሃል አሉ:: ይሄ ፀሃይ የሞቀው ሃቅ እያለ ተስፋዬ የፕሬስ መምሪያ ሃላፊነት ይገባዋል ያለ አቶ በረከት ጠላቴ ሆኖ ካገር አስወጣኝ ስትል ትዝብት ነው ትርፉ። ይህ ጉዳይ አንተው እራስህ ብር መመንተፍህን በመፃፍህ በብዙ ቦታ ሳታውቀው ስለገለፅከው ብዙ አልሄድበትም።

## ቅንጭብጫቢዎች

ከማጠቃለሌ በፊት የተወሰኑ ነገሮች የቀሩ መሰለኝ።ካልተቀየምከኝ ካንተው ጭብጥ ወስጄ ቅንጭብጫቢ የሚል ርዕስ ሰጠሁት::

ስለ ሰላም አውቶብስ ያነሳሽው ጉዳይ አለ። ይህ ጉዳይ ለህወሓትና ለትግራይ ልማት ማህበር ባዳ በሆነ ሰው ቢፃፍ ብዙ ችግር አልነበረውም። የህወሓት ታጋይና አባል ሆኜ በከፍተኛ ስልጣን ላይ ነበርኩ ከሚል ሰው እንዲህ አይነት ነገር ስሰማ ግን ለኔ አይነቱ ሰው ተስፋዬ የህወሓት ምርኮኛ ሆኖ ተቀላቀለ፣ ምርኮኛ ሆኖ ፈረጠጠ የሚል ድምዳሜ ከማጠናከር ውጭ ሌላ ትርጉም የለውም። ነገሩ እንደዚህ ነው የሰላም አውቶቢስ አክስዮን ማህበር በጣም በማከብረው በሚቹ በአቶ አርአያ ዘሪሁን የትግራይ ልማት ማህበር ሊቀመንበር በነበረው የተቋቋመ ድርጅት እንጂ አቶ ስዩ ይመራው በነበረው ትእምት ስር የተደራጀ አልነበረም። አቶ ስዩ ድንበር ዘሎ የሰላም አውቶብስ ስራ የመራበት ግዜም ታሪክም የለም። ይህን ለማጣራትም ለማወቅም አለመሞከርህ ያስተዛዝባል ብቻ ሳይሆን ቅንጭብጫቢ ፅሁፍህን ታማኝነት እንዳይኖረው ያደርገዋል።

ከአቶ በረከት ዕልቅና ወጥተህ ወደ አቶ አለም ሰገድ እልቅና የተሸጋገርክበት ሁኔታ የገለፅክበትም መንገድም እንዲሁ አስቂኝ ነው። መጀመሪያ ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ የመንግስት ሚዲያዎች አስተባባሪ አቶ በረከት ነበር። አንተም በመንግስት ሚዲያ ውስጥ ስለነበርክ አቶ በረከት ነበር አለቃህ። ያ ስራ እያስደነበረ ስላስቸገረህ ከፕሬስ ሀላፊነት ወደ ግል ኢምፓየርህ ስትሸጋገር ይህ

ኢምፓየር በድርጅት ሚዲያ ውስጥ እንዲተዳደር ስለተወሰነ አለቃህ የድርጅት ሚዲያ ይመራ የነበረው አቶ አለም ሰገድ ገብረአምላክ እንዲሆን ተወሰነ። አንተን ከበረከት ግምገማ ነፃ ለማውጣት የተደራጀ፣ የተዋቀረ አካል አልነበረም። ይህ ስህተት በመንግስት ሚዲያና በድርጅት ሚዲያ መካከል የነበረውን የአደረጃጀት ሁኔታ የማታውቅ መሆንህን ከመግለፅ ውጭ ሌላ ፋይዳ ያለው ነገር የለውም። አንተ ግን ከአገር የወጣህበትን ምክንያት ለማመቻቸት ስትል ይህን ድራማ እየፈጠርክ ለመፃፍ ፈለግክ።

የካቲት 11፣ ከኛ ከትግሬዎቹ የፊታችን መለያ 11 ቁጥር ጋር እንዲመሳሰል የተቀየሰ ቀን መሆኑን አቶ ገብረመስቀል ሃይሉ እንደነገርህ አወሳኸን። ተስፋዬ በመፅሃፍህ መግቢያ አካባቢ በህይወት ለሌሉ ታማኝ ለመሆን እንደጣርክ ገለፅክ፣ ይህን ተረት ተረት ግን ሚች አቶ ገብረመስቀል እንደነገረህ ስትነግረን አቶ ገብረመስቀልን የሚያውቁ የህወሓት ታጋዮች ብቻ ሳይሆኑ ያኔ ድሮ በተማሪው እንቅስቃሴ ወቅት አቶ ገብረመስቀልን በአ/አበባ ዩኒቨርስቲ የሚያውቁት አንጋፋ ታጋዮች ልባቸው ይደማል:: በህወሓት ውስጥ አቶ ገብረመስቀል በመሰረታዊ ቁምነገሮች እንጂ እንዲህ አንተ እንደምትነግረን ተረት ተረት የሚያወራ ሰው አልነበረም። የትግሉ መስራች ጓዶች ደደቢት ሲገቡ አቶ ገብረመስቀል እዛ አልነበረም። የህወሓት ልደት በ11 ቁጥር ዙሪያ እንዲሆን ቢወሰን ኖሮ በዚህ ስነአመክንዮ መሰረት በ11ኛው ቀን በ11ኛው ወር በ11ኛው ሰዓት ወዘተ የሚል ይሆን ነበር። ያ ግን አልሆነም። በህይወት ለሌለ ሰው ታማኝ ባለመሆን ታለቁን ሰው እንዲያ ልታሸከመው መከጀልህ ግን ቁስል ነው።

በአቶ አየነው ቢተውልኝ ላይ የተጠቀምክበት ሁኔታም ተመሳሳይ ነው:: አቶ አየነው ቢተውልኝ በህይወት የለም። ጥሩ ኢትዮጵያዊ ነበር። ምሁርም። አንተ ግን አቶ አየነው ትግራይ ውስጥ ሊሰራ ታቅዶ ስለ ነበረው የባቡር ሃዲድ እንዳወራህ ተረክልን። ህወሓት ኢህአዴግ ትግራይ ውስጥ የባቡር ሃዲድ ለመዘርጋት እቅድ እንደነበረው ነገርከን፣ - የሻዕቢያ ተረት ተረት - አሁንም በህይወት በሌለ ሰው ላይ ቀለድክ።

የደህንነት ሰነዶችን በሚመለከት ያቀረብከውም ከዚ የተለየ አይደለም። አንድ ቦታ ላይ ሳት ብሎህ የሪፖርተር ዋና አዘጋጅ አቶ አማረ አረጋዊ ከድርጅት ሚዲያ በላይ ለደህንነት ሰነዶች የቀረበ ሰው ነበር ብትልም ያ ጠንቃቃው አቶ ክንፈ ያለ ከልካይ የደህንነት ሰነዶች እንደልቤ እንድፈነጭባቸው በሩን ከፍቶልኝ ነበር ማለትህ ግን አሁንም በህይወት በሌለ ሰው ቀላመድህ።

ሌላው የገረመኝ ጉዳይ የተክሉ ተክላይ ጉዳይ ነው የኢትዮጲያ ሰው ስም ሲያወጣ ጠንቃቃና ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ነው። የኛ ሰው ምኞቱን፣ ፍላጎቱንና፣ ተስፋውን የሚገልፀው አብዛኛው ለልጁ በሚሰጠው ስም ነው። እኔ እስከማቀው ድረስ ተኽሉ - የእርሱ ተክል፣ ተኽላይ ማለት ደግሞ የኔ ተክል ማለት ነው። በነዚህ ስሞች መካከል የእርሱና የእኔ የሚል ባለቤትነትን ከሚያመለክት ስም በስተቀር ልዩነት የላቸውም። ታድያ ተኽሉ ተኽላይ የሚባል ገፀባህርይ ከየት ተፈጠረ? ተኽሉ ተኽላይ የሚባል ታጋይ በፕሬስ መምሪያ የሚሰራ ሰው ነበር? ምን ክፍል ውስጥ? አስቂኝ ሰው። የሌለና ያልነበረ ሰው ፈጥረህ ስታስቀን ከረምክህ። በአጭሩ ተኽሉ ተኽላይ የሚባል ሰው የለም፣ አልነበረም ያንተ የፈጠራ ሰው ነው::

## ማጠቃለያ

ሳላውቀው ብዙ ነገር ጠቃቀስኩ ተስፋዬ ባጭሩ አንተ በኢህአዴግ ውስጥ ታቅፈህ የኖርክ ለምድ የለበስክ ቀበሮ ነበርክ:: ተስፋዬ ስለ ኢህአዴግ የምታውቀውም የምታጋልጠውም፣ የምትደብቀውም ሚስጢር የለህም:: የምታውቀው ቅንጭብጫቢ ነው። ይህን ደግሞ አሁን ዘረገፍከው። በኢህአዴግ ዓይን ተስፋዬ እንደ አንድ ሪፖርተር የሚታይ እንጂ አንተ እንቀላመድከው ከፍተኛ የኢህአዴግ ባለስልጣን አልነበርክም ሆነህም አታውቅም። በቃ እፎይታ ጋዜጣና መፅሔት የሚያዘጋጅ ተራ ጋዜጠኛ። አራት ነጥብ።

ይህን መልስ በመፃፌ የተወሰነ ቀልብ እንድታገኝ የሚያግዝህ መሆኑን ባውቅም ምንን ምን ካላሉት ሆኖብኝ መልስ እንድሰጥህ ተገድጃለሁ:: ይህን መጣጥፍ ስሞነጫጭር አላስፈላጊ ሆኖ ያስቀየምኩት ሰውም ሆነ አካል ካለ አስቀድሜ ይቅርታ እየጠየቅኩ ልሰናበትህ። አስፈላጊ ከሆነ ስለ አ/አበባ ምሽት ህይወትህ ተመልሼ እመጣ ይሆናል::